ፓኖራማ ቁጥር 66

የትዝብት አድማስ

መጋቢት 27 ቀን 2001 ዓም

## በራሷ አረም አጋዧን በእባብ ታስፈራራለች

ባሏን በሞት በመነጠቋ ምክንያት፥ ረዳትና አጋዥ አለመኖሯን የተረዱላት ጎረቤቶቿ ተሰብስበው የወጀዷን ቡቃያ እያረሙላት እያሉ ፥ እርሷ ግን እባብ ይዛ እያስፈራራች አበራረቻቸው ሲባል አንሰማ ነበር ። ይህ የቆየ ተረት በመሆኑ ፥ ምናልባት ብዙዎቻችን ላናስተጋባው እንችል ይሆናል ። ዛሬ ግን ይህ ተረት ወደ ዕውነትነት በመለወጥ ላይ ይገኛል ። የሀገራችንን አሜካላና ተባይ ለመንቀል በሚደረገው ሂደት ፥ ተስማምቶና ተባብሮ የሀገርን ደመኛና ተውሳክ ማስወገድ ሲገባ ፥ ተባይና አራሙቻውን እየተው ፥ አራሚዎቹን በማጥፋት ተባዮቹን ግን በማፋፋት ላይ ይገኛሉ ። ዓላማን ዒላማ አድርጎ በሀገር ጠላቶች ላይ መተባበር ሲገባ ፥ ዓላማውን በትክክል ካለመረዳት የተነሳ ፥ የሀገርን መከታና የሕዝቡን አለኝታ የሆነውን ኃይል፥ የጥቃታቸው ዒላማ አድርገው ይንቀሳቀሳሉ ። ግልፅ የሆነ ዓላማን አንግቦ መንቀሳቀስና በዓላማ ቢስነት ዕውር- ድንብሩን መንከላወት የተለያዩ መሆናቸውን እንኳ በቅጡ መረዳት አልተቻለም ። መነሻና መድረሻውን አውቆ በመገስገሻው ሂደት ውስጥ ዓላማውን አስገብቶ ወዳጅና ባላንጋራውን ለይቶ የባላንጋራውንም እንቅስቃሴ ዒላማ በማድረግ ቁርጠኛና ወሳኝ ትግል ማድረግ ሲቻል ፥ ይህ ግን እስካሁን አልተቻለም። ከዚህ ይልቅ፥በአንፃሩ የሀገር ጠላቶችን ዕድሜ ማስረዘም የዓላማ ቢሶች ቀዳሚ ተልዕኮ ሆኖ ቀርቷል ። ይህ እንዲህ ሆኖ ሊቀጥል አይገባውም ። አዲስ የትግል ምዕራፍ ሊከፈት የግድ ይላል ።የሀገሪቱም ሁለንተናዊ ሁኔታ የተለየ አቅጣጫ አማትሮ መንቀሳቀስን ይጋብዛል ። ጠላትንና ወዳጅን ለይቶ ካለማወቅ የተነሳ፥ ማን ከማን ጋር ሊያብር እንደተነሳ ሳይታወቅ፥የትግሉንም የአጭር የመካከለኛና የዕሩቅ ርምጃ በሚገባ ተለይቶ መፈረጅ ለወሳኝ ትግል መሠረት ነው ። አሁን የሚታየው ሁኔታ እንዲያው የዳበሳ ጎዞ መሆኑን በድፍረት አምኖ በመቀበል ድፍረትን አንግቦ ድፍረትንና መሥዋዕትን የሚጠይቅ የደፋር ሥራ ካልተጀመረ ፥ ወያኔዎቹ ኢትዮጵያን በድዳቸው እየገዘገዙ እንደሚያጠፏት መጠራጠር አይቻልም ። ሀገርን ከባዕዳን ተፅዕኖና ከዘረኞች የጭቆና አገዛዝ ነፃ ለማውጣት የሚቻለው ፥ በራስ አረም እባብ ይዞ በማስፈራራት ሳይሆን ፥ ከወገን ጋር አብሮ ፥ ሰላዩንና አድር

ባዩን ለይቶና አግልሎ ፥ በሀገራችን ዋናና ስትራተጃዊ ጠላት ላይ ተባብሮ መነሳት ሲቻል ብቻ ነው ። ሌላ አማራጭ ሊኖር አይችልም።

ወያኔዎቹ ዓላማቸው ግብ እንዲመታላቸው ያልፈነቀሉት ድንጋይ፥ ያልበጠሱት ቅጠል ፥ ያላንኳኩት በራፍ፥ ያልቀጠፉት ቅጥፈት፥ያልፈፀሙት ጥፋት፥ ያልጫሩት እሳት፥ያላጠፉት ሕይወት አልነበራቸውም ። በሀገራቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ ያለፈፀሙት ወንጀል፥ በራሳቸው በትግራይ ብሄር ሳይቀር ያላመጡት ውርደትና ሀፍረት የለም ። ያልሆኑትን ለመሆን ሲሉ ያልወሸከቱት መወሸገት አልነበረም። " **ዓላማህ ግብህን እስከመታልህ ድረስ ማነኛውንም ሁሉ አድርግ፥ የመጨረሻው ውጤት ጥፋትህን ሁሉ ይሽርልሃል**" ሲል በ14ኛ ምዕተ ዓመት የነበረው ማኪያ-ቬሌ የተሰኘ የኢጣሊያ የፖለቲካ ጠበብት የተናገረውን ቲዎሪ ቃል በቃል በተግባር የተረጎሙ ናቸው ስንል፥እያንገፈገፈን ነው። " ይሉኝታ የራስ ኃይሉን ቤት የፈታ" የሚለውንም ይትብሃል በሚገባ ተጠቅመውበታል ማለት ይቻላል። ይህንን ሁሉ መጥቀሳችን ፥ የእነርሱን መሰሪነት ለማስታወስ ሳይሆን፥ የጥፋት ዓላማቸውን ከግቡ ለማድረስ ፥ ኢትዮጵያን አጥፍቶ ከመጥፋት ወደኋላ የማይሉ መሆናቸውን በአትኩሮት ለመግለፅ ስንል ነው። " የሰው ሞኞ አንደ እንጨት ያስራል" እንዲሉ ፥ ታዲያ ወያኔዎቹ ኢትዮጵያን ለመከፋፈል ሲሉ የተጠቀሙበትን ሁሉ ተጠቅማችሁ ለምን እናንተስ ሀገራችሁን አላዳናችሁ ም? የሚል ጥያቄ ተደጋግሞ ይጠየቃል። ይህንን ጥያቄ በቀላሉ ለመመለስ ከመቃጣት፥ ሞኝ ሰው አንድ እንጭት ለማሰር እንደሚከጅለው ቀላል አይሆንም ብሎ ማለፍን እንመርጣለን።

የሀገራችን ስር የሰደደ ችግር በአንድ የአዝመራ ወራት እንደሚነቀል አረም ወይም እንደ አጨዳና ነዶ መሰብሰብ ቀላል አይደለም ። በሦስት ተፈራራቂ ሥርዓቶች ተከማችቶ የደለበ ነው ። የተገነባውን በማፍረስ፥አዳዲስና ተጨማሪ ጥፋትን መፈፀምን እንጅ፥ ችግርን ለመቅረፍ የሚደረግ ጥረትና ዓላማ አይታይም ። ይህም የሚፈፀመው ከፍላጎት ማጣት ብቻ ሳይሆን ፥ ጭራስ ዕውቀትና ችሎታ ካለመኖርም ጭምር ነው ። ፈቃደኝነትና ችሎታ ፍላጎትና ዕውቀት ከሌሉ ደግሞ፥ እንኳንስ የኢትዮጵያን ዘርፈ-ብዙ ችግር መቅረፍ ቀርቶ የግል ሕይወትንም ቢሆን መምራት አይቻልም ። በተለይ ደግሞ ፥ መልካም ተግባር ለመፈፀም ጥረት በሚደረገበት ሂደት ፥ሰዎች በራሳቸው አረም እባብ ይዘው የማስፈራራት ጥረት ካደረጉ! በራስ ጉዳይ ላይ በእባብ የሚያስፈራሩ ክፍሎች ይህንን የሚያደርጉት በሁለት ምክንያቶች ሊሆን ይችላል ተብሎ ይገመታል ። አንደኛው እኔ ካልሰራሁት፥እኔ ከሌለሁበት ምን-ተዳየ ሁሉ ነገር ገደል ቢገባ ከሚል ሲሆን ፥ ሁለተኛው ደግሞ ፥ የኢትዮጵያ ጉዳይ ጉዳያችን አይደለም ። ካለው ሥርዓት ጋር ዕድላችንን አጣምረን

ተጠቃሚዎች መሆን አለብን የሚል ነው ፡፡ ሁለቱም ሀገራዊም ይሁን ሕዝባዊ ፍቅር ይኖራቸዋል ተብሎ የሚታሰብ አይሆንም ፡፡ የአንድ ሀገር ዜጋ ነኝ የሚል ፍጡር፥ የሀገሩም ይሁን የሕዝቡ ፍቅር ከሌለው ደግሞ ፥ በደመ-ነፍስ ከሚንቀሳቀስ እንስሳ ተለይቶ ሊታይ ይገባዋል ለማለት ያስቸግራል ፡፡ በእንስሳና በሰብዓዊ ፍጡር መካከል አሉ ከሚባሉ ልዩነቶች መካከል አንዱ፥ ከእለት ጥቅምና ፍጆታ በላይ ማስብ ወይም አለማሰብ ነው፡፡እንስሳ ከዕለት ከርሱ በላይ አለማሰቡ ፥ የአህያና የሰርዶው ተምሰሌት በቂ ገላጭ ይሆናል፡፡ሰዎች በሰብዓዊ ነታቸው ብቻ ለነገ ማሰብ ካልቻሉ ታዲያ የመኖር/ ያለመኖር ትርጉም እምኑ ላይ እንደሆነ ለይቶ ማስቀመጥ ያስቸግራል ፡፡ ለመኖር ብቻ ሲባል የሚኖረው ኑሮና ለመኖር ብቻ ሲባል አለመኖርን መምረጥ ፥ የሰውን ልጅ ከእንስሳ ለይቶ ሰብዓዊ ክብር እንዲጎናፀፍ ያደርገዋል ፡፡ለዚህ አባባል እንደ መልካም አርዓያ የሚጠቀሱት አርበኞችና ሰማዕታቱ ናቸው ፡፡ የሀገር መሪም ይሁን ወይም የድርጅት መሪ ከተሆነ ዘንዳ ፥ የኋላ ልጅ ይጨነቅበት ወይም የሚተካው ትውልድ ያስብበት፥ በሚል የሥነአዕምሮ እሴት ውስጥ መግባት፥ አሁን ያለውን ሀገርና ትውልድ መበደል ብቻ ሳይሆን፥ በሚቀጥለው ሀገርና በተኪው ትውልድም ላይ የሞት ፍርድ እንደ መፍረድ ይቆጠራል ፡፡

በአለፉት አረባ ዓመታት ውስጥ የተለዋወጡትን ሥርዓቶችና አራማጆቻቸው አንድ አካል አንድ አምሳል ከሚያደርጋቸው አንዱ፥ ሦስቱም ለነገዋ ኢትዮጵያና ለተተኪው ትውልድ ለማሰብ አለመቻላቸው ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም ፡፡ ያማ ባይሆን ኖሮ ፥ የሀገራችን ሁኔታም ይሁን የዜጎቿ ችግር አሁን ከደረሰበት አስጊና አሳሳቢ ደረጃ ባልደረሰም ነበር፡፡ ይህ ክስተት ደግሞ ለሀገር መሪዎች ብቻ ሳይሆን፥ምሁራኑንም ፥ የተቃዋሚ ክፍሉንም ጭምር የሚመለከተውና የሚዳስሰው ነው፡፡ በተለይ ደግሞ፥ የሁኔታዎችን ሂደት በተወሰነ የጊዜ ቀመር አስገብቶ መገምገም የሚቻል ከሆነ፥ በአለፉት 18 ዓመታት ሀገራችን ለወደቀችበት የህልውና አደጋ ሁሉም እንደ የድርሻው የየራሱን ተጠያቂነት መቀበል ይኖርበታል፡፡ ይህም ግምገማ ፥ በፈፀመው ተግባር ብቻ ሳይሆን ፥ ሳይሰራ በመቅረቱም ጭምር ያለውን ያጠቃልላል፡፡ ምክንያቱም፥ እየታገሉ የሚዋደቁትን ማብጠልጠልና መክሰስ ብቻ ሳይሆን ከእነርሱ የተሻለ መሥዋዕት በመክፈል ሀገሪቱን ለማዳን በሚደረገው ትግል የበለጠ አማራጭ ሆኖ ባለመገኘትና አማራጭም ይዞ ባለመቅረብም ጭምር ነው ፡፡ ኢትዮጵያ የሁሉም ዜጋ መሆን አለባት እስከተባለ ድረስ፥ ለአካለ መጠን ከደረሰው ወጣት አንስቶ እስከ አዛውንቱ ድረስ በሀገሩ በኢትዮጵያ በጥፋቱም ይሁን በልማቱ ፥ በቀጥታም ይሁን በአንደምታ ተጠያቂነትና ኃላፊነት ስለአለበት ነው ፡፡አለዚያማ መፈክሩ መንግሥት ይለወጥ መባሉ ብቻ ሳይሆን ፥ ሕዝብ ይለወጥልን ወደሚለውም ፈዝና ቧልትም ሊያመራ ስለሚችል ነው፡፡ ይህ ደግሞ፥መለስ ዜናዊና ሙአማር ቀዛፊ በውይይታቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ከኢትዮጵያዊነት ወደ ዐረባዊነት እንደለውጡት ማለት ይሆናል፡፡




EthioLion.Com

በወቅቱ የሀገራችን የፖለቲካ መልከዓ-ምድር ተውኔት የሚጫወቱት የፖለቲካ ተዋንያን ከሞላ ጎደል ያተኮሩት ፥ በጊዚያዊው ክስተት ላይ ብቻ መሆኑ የሚካድ አይደለም ። ያም ሆኖ ግን የለውጥ ውጤት ሊያስመዘግቡ አልሆነላችውም። የተሻለ ለውጥ ማስመዝገብ ቢችሉ ኖሮ ቢሆን እንኳን፥በጊዚያዊው ላይ ብቻ ማተኮራቸው አያስወቅሳቸውም ነበር።ምክንያቱም ፥ የሀገሪቱን ቀንደኛ ጠላቶች ማስወገድ ችለው ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሁኔታውን ቢያመቻቹለት፥ ሕዝቡ የመረጠውን ሥርዓትና መንግሥት ማቋቋም ይችል ነበር። እስካሁን በሚደረግው ማነኛውም ፀረ ወያኔ እንቅስቃሴ ምልዐተ - ሕዝብን የሚያሳትፍ ዕድል አልተከሰተም ። የነገውን አሳታፊ ዲሞክራሲ በአስተማማኝ መልኩ ለማረጋገጥ፥ ዛሬ በትግሉ ሂደት ሕዝቡ እንዲሳተፍና ሙሉ ትብብሩን እንዲያሳይ ማድረግ አስፈላጊ ለመሆኑ ብዙ ትንታኔ የሚያስፈልገው አይደለም። አንዱ የሰራውን ሌላው እንዳያፈርሰው፥ በርካቶቹ የደከሙበትን ጥቂቶቹ እንዳያበላሹት፥ሁሉም በራሱ አረም እባብ ይዞ እንዳያስፈራራ ዋስትና የሚሆነው፥ በሀገር ጉዳይ ሁሉም መሳተፍና የትግሉም ሂደት አካል መሆኑን ሲያረጋግጥ ነው ። ይህ ደግሞ ሰፋ ተብሎ ሲታይ፥ ለነገዋ ኢትዮጵያ ዕድል ብሩኅ ተስፋና ራዕይ ያለው የፖለቲካ መሠረት ለመጣል ዋስትና ይሆናል ። በራስ ሀገርና ሕዝብ ትግል ላይ እባብ ይዞ ማስፈራራት ፥እንደ ብሔራዊ ወንጀል እንጅ ፥ አንዳንዶቹ እራሳቸውን እንደሚያታልሉት የፖለቲካ ዕውቀት አይደለም ።

የወያኔን አገዛዝ ለማውደም ቆርጠን በጋራ እንነሳ !

EthioLion.Com